# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

**<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ሐገረ ስብከት ካህናት፣ ሰባኪያን፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ኅብረት፣ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ደቀ መዛሙርት ና ምሩቃን እና የመንፈሳዊ ማኅበራት ተወካዮች እና በመስከረም 4 ቀን በዲስ አበባ ሊካሄድ የታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪዎች ሰላማዊ ሰልፉን አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ</u>**

በአገራት የታሪክ ግንባታ ላይ የሃይማኖት የተቋማት አስተዋጽኦ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በተለይ ተቋማቱ ከአገራቱ እድሜ የማይተናነስ የዘመን ርዝማኔ ሲኖራቸው ከሚተረከው የአገሪቱ ታሪክ ላይ የእነርሱ እጅ ያልገባበትን፣ አሻራቸው ያላረፈበትን ዘርፍ ለይቶ ለማውጣት እስኪከብድ ድረስ የአገር ታሪክ እና የሃይማኖት ተቋሙ ታሪክ እንደ ድርና ማግ የተገመደ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

በአገራችን በኢትዮጵያ ያለውም እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ የሌሎቹ እምነቶችና ባህሎች አስተዋጽኦ እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያን ያለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማሰብም ሆነ የወደፊት እጣዋንም በአዎንታዊ መንገድ መተለም ፈጽሞ አይቻልም፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ የቤተ ክርስቲያኗን ስም ሳያነሱ ለመተረክ መሞከር እስከሚያዳግት ድረስ ቤተ ክርስቲያን የአገር የልብ ትርታ ሆና ኖራለች፡፡ በአገራችን ስልጣኔ ላይ ዘርዝሮ ለመጨረስ የሚያዳግት አሻራን አሳርፋለች፡፡

ምእመኗን ሌት ከቀን ስለሳላም በማስተማር እርስ በእርሱ በመከባበር እና በፍቅር ከመኖር አልፎ የሌላውን እምነት እና ባሕል አክብሮ እንዲኖር አድርጋለች፡፡ ትምህርት የመንግስት የፖሊሲ አካል ባልነበረበት ዘመን ትምህርት ሚኒስተር፣ ባህል እና ቱሪዝምን ማሳደግ ቦታ ባለገኘበት ዘመን የባህል እና የቅርስ ጠባቂ ሆናለች፡፡ አገር በተወረረበት ዘመን ጽላቷን ሳይቀር ተሸክማ ከጦሩ ፊት ተሰልፋለች፡፡ ዓለምና አገር ለሥነ- ጽሑፍ፣ ለሥነ ሥዕል፣ ለኪነ- ጥበብ፣ ለኪነ-ሕንጻ እና መሰል ጥበቦች ባእድ በነበረበት ዘመን ለአገራችንና ለዓለም እስከ ዛሬ የሚመራመርበትን የጥበብ ፋና አብርታለች፡፡ ከግብርና እስከ ሥነ ከዋክብት፣ ከዘመን አቆጣጠር እስከ መድኃኒት ቅመማ፣ ከሕግ ቀረጻ እስከ ደን ልማት፣ ከቤተሰብ አስተዳደር እስከ ስነ-መንግሥት፣ ከዜማ ፈጠራ እስከ ማኅበራዊ እሴት ግንባታ ያላትን ኃብተ ጥበብ ሁሉ ለኢትዮጵያ እያበረከተች ከራሷ ሕልውና በላይ ስለ አገር ኖራለች፡፡ በየትኛውም የታሪክ ዕይታ እና መንገድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሊደራደር ከመጣ አካል ጋር ለውይይት የተቀመጠችበት ዘመን የለም፡፡ እርሷ እየነደደች እና እየከሰመች አገርን አጽንታለች፡፡ ለዚህ ውለታዋ ግን ወሮታ የጠየቀችበት፣ ለዚህ መስዋእትነቷ ዘካሪ የሻተችበት ዘመን የለም፡፡

ይሁንና ወርቅ ላበደረ ጠጠር እንዲሉ ዛሬ ዛሬ በኢትዮጵያ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጡት የመንከስ ያህል አጠያያቂ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ ካህናት እና ምእመናን ተወልደው ባደጉባት ምድር ታርደዋል፣ ያፈሩት ሃብት ንብረትም ሁሉ የእሳት አሊያም የቀማኛ ቀለብ ሆኗል፡፡ ከሕጻን እስከ አረጋዊ፣ ካልጋ ቁራኛ እስከ ነፍሰ ጡር ድረስ ኦርቶዶክሳዊያን አንስቶች በአሰቃቂ ሁኔታ ተደፍረዋል፡፡ መከራ የበረታባቸው ለዘመናት የኖሩበትን ቀየ ለቀው ወደማያውቁት ቦታ ተሰደዋል፡፡ በጠረፉ የኢትዮጵያ ክፍል የተጀመረው ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ ጥቃት ወደ መሃል ከተማ በሚያስደንቅ ፍጥነት እየገሰገሰ ይገኛል፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እና ምእመናን ከዛሬ ነገ ጉዳዮን የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ይፈቱታል በሚል ተስፋ የየመንግስት ተቋሙን በር ስናንኳኳ ቆይተናል፡፡ ቢሆንም ጩኸታችንን በሚፈለገው ፍጥነት የሚሰማ፣ የሚፈታም ሆነ መልስ የሚሰጥ አካል አልታየም፡፡ ከዚህም ሲያልፍ ለሁሉም ችግር ኃይል እና ነውጥ መፍትሔ ተደርጎ በሚወሰድበት በዚህ ዘመን ለሰላም እና ለአገር ባለን ጥልቅ ፍቅር ሕጋዊ ጥያቄ አቅርበን በሕግ ከተሾመው ሕጋዊ አካል ሕጋዊ መፍትሔ መፈለጋችን በሚያሳዝን ትርጉም እየተሰጠው እና ከፍርሃት እየተቆጠረ መሳለቂያ ከመሆን የዘለለ ጠብ የሚል መፍትሔ ሊመጣ አልቻለም፡፡

በመሆኑም እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ አበባ ከተማ የምንገኝ ካህናት፣ የሰባኪያን እና ዘመሪያን ኅበረት፣ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ፣ የመንፈሳዊ ማኅበራት ማኅበራት፣ የወጣቶች እና የጎልማሶች ማኅበራት ኅብረት፤ የነገረ መለኮት ምሩቃን እና የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች ኅብረት፡ በመስከረም 4 ቀን 2012 ዓ/ም ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ጥሪ ማድረጋችን ይታወቃል፡፡

ይህ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ ከቀረበበት ማግስት ጀምሮ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ራስ ከሆነው ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጀምሮ፣ በአገርም ይሁን በውጩ ዓለም ያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ በአንድ ልብና መንፈስ በታላቅ ቁጭት ያሳየውን የመንፈስ ዝግጅት እና ተነሳሽነት በቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ ነበር፡፡ ከብረት የጠነከረው ይህ የኦርቶዶክሳዊያን ኅብረት እና ተነሳሽነት እናቱ ስትታመምበት እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ አርፎ እንደማይተኛ እና የትእግስቱን ያህል ቁጣውም ምን ያህል የገዘፈ እንደሆነ ለብዙዎች ትልቅ ትምህርት የሰጠ እንደሆነ ሁሉም የተረዳው እውነታ ነው፡፡

በተጨማሪም ስለ አገር ሰላም፣ ስለ ሕዝቦች አንድነት፣ ፍትሕና እውነተኝነት የሚገዳጋቸው የሌሎች እምነቶች ተከታይ ወንድም አኅቶቻችን ሁሉ ህመማችንን ተጋርተው ከጎናችን እንደሚቆሙ እየገለጹልን ይገኛሉ፡፡

ዛሬ በጋራ መሰለፋችን እና ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ክብር በአንድ መቆማችን በብዙ ልመና ሊከፈቱ ያልቻሉ ጠንካራ በሮችን ለማስከፈት ችሏል፡፡ በዚህም መሠረት አስተባባሪ ኮሚቴው 1. ጳጉሜ 5/ 2011 ዓ.ም ከጠቅላይ

ሚኒስተር ጽ/ቤት ተወካይ፣ ከፌድራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ ከአዲስ አበባ ም/ከንቲባ እና ጽ/ቤት ተወካዮች ጋር 2. ጳጉሜን 6/2011 ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር 3. መስከረም 2/2012 ዓ/ም ከኦሮምያ፣ ከደቡብ፣ ከአማራ፣ ከሶማሌ ክልሎች ርዕሳነ መስተዳድሮች ጋር በአካል ተገናኝተን ውይይቶችን የጀመርን ሲሆን ከሐረሪ እና ቤኒሻንጉል ክልሎች እና ከድሬዳዋ መስተዳድር ጋር ለውይይት ቀጠሮ ተይዟል፡፡ 4. መስከም 2/2012 ዓ/ም ከፌድራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ አዲስ አበባ፣ ኦሮምያ፣ አማራ፣ሱማሌ፣ ቤኒሻንጉል፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ፖሊስ ኮሚሽነሮች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ በነዚህ ውይይቶችም ከአሥር ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ኮሚቴው ይዞት የተነሳውን እና ቤተ ክርስቲያኗ ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት ለመፍታት በየክልሎቹ ዝርዝር ማስረጃ ቀርቦ ውይይት እንዲደርግባቸው እና ለጥቄዎቹምምላሽ እንዲሰጣቸው እና በቀጣይ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ ከላይ ከተጠቀሱት የመንግስት አካላት ጋር ውይይት በማድረግ በባለቤትነት ችግሩን ለመፍታት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ .

በመንግስት ጥያቄያችንን ሁሉ ይመልሰዋል የሚል እምነት ባይኖረንም በየደረጃው ያሉ አካላት ቸልታ እና የማናለብኝነት ስሜት ወጥተው ለቤተ ክርስቲያናችን ዘብ ሲቆም መመልከት እንሻለን፣ አገራችን ደጋግመን እንደምለው አንዳንዱ የፈለገውን ከሕግ የተጻረረ ተግባር በተለይ በኦርቶዶክሳዊያን ላይ እየፈጸመ ያለአንዳች ጠያቂ የሚኖርባት ሌላው ደግሞ ስለአገር እና ስለአንድነት በሚወስደው ኃላፊነት የተሞለበት አካሄድ እየተገፋ ከሌሎች ጋር ሲገነባት በኖራት አገር ላይ ባይተዋር ሆኖ የሚሰደድባት አገር መሆኗ ተቋጭቶ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ እጁን ያነሳ ሁሉ የሚጠየቅባት፣ ጣቱን የቀሰረው ሁሉ የሚሰበሰብባት ለፍትህ የሚተጋ መንግስት ያለባት አገር ስትሆን መመልከት ሕልማችን ነው፡፡

እየጮህን ያለነው የኦርቶዶክሳዊያን ብቻ ሰላም ይከበር ብለን አይደለም፣ የእምነት ነጻነት ሰፍኖ አገራችን በእምነታቸው የተነሳ የተደፉ አንገቶች ቀና ብለው ሁሉም በመከባበር የሚኖርባት ሰላማዊ አገር ስትሆን ለመመልከት ነው፡፡ ይህ እስኪሆን ድረስ ከራሳችን እምነት ተከታዮች ጎን ብቻ ሳይሆን በእምነታቸው የተነሳ ከሚገፉት ጎን ሁሉ በማስመሰል መንፈስ ሳይሆን ከአያት ቅድም አያቶቻችን በወረስነው ለፍትህ የመወገን መንፈስ አብረን እንቆማለን፡፡ ለዚህ ነው ጉዟችን ኦርቶዶክስን ብቻ ሳይሆን አገርን ጭምር ለመታደግ የታለመ ነው የምንለው፡፡ በመሆኑም ስለሃይማኖታችን እና ሥለአገራችን ሰላም ስንል እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎቻችን እንኪመለሱ ድረስ ትግላችንን በሰላማዊ መንገድ እንደምንቀጥል ቃላችን የጸና ነው፡፡

የተከበራችሁ ኦርቶዶክሳያን እና ኦርቶዶክሳዊያት በዚህ መንፈስ እና ዓላማ ተቃኝቶ የተጀመረው የኀብረት ጉዟችን ከገዳም እስከ ከተማ ድረስ ካሉ አባቶች ጋር በመመካከር እና በጸሎታቸው በመታገዝ ከዚህ አድርሰነዋል፡፡ በብዙዎቻችሁ ውስጥ ያለው የመንግስት አካላት ቃል ከመግባት የዘለለ እርምጃ ላይሄዱ ይችላሉ የሚለው ስጋት ግን በእኛም ውስጥ ስላለ፤ ከላይ ያልናቸውን ጥያቄዎቻችንን በቅድመ ሁኔታ ጭምር አቅርበን እስከንወያይ እና

የሚመጣውን ተግባራዊ ለውጥ ለመመልከት እስክንበቃ ድረስ ለመስከረም 4 ቀን 2011 ዓ/ም የጠራነውን ሰላማዊ ሰልፍ በሁለት ወራት በመግፋት የተገባልን ቃል የማይተገበር ከሆነ አሊያም የሚያረካ ካልሆነ ለጥቅምት 30 ቀን 2012 ዓ/ም ሰላማዊ ሰልፉ የሚደረግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

እኛ የዚህ ሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪዎች በሚደረገው በየትኛውም ውይይት ላይ ከራሳችን ፍላጎትም ይሁን አንዳንዶች ከሚሰጉት የፍርሃት መንፈስ በጸዳ ስሜት የቤተ ክርስቲያናችንን እና የእናንተን የእምነቱን ተከታይ ኦርቶዶክሳያን ፍላጎት እና ጥያቄ ብቻ አስቀድመን የምንቆም መሆናችንን በህያው እግዚአብሔር ስም ቃል እየገባን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ልጆች ሁሉ ያሳያችሁት ተነሳሽነት እና ኅብረት ሳይሸራሸፍ ለችግራችን ሁሉ ቁልፍ መፍትሔ በሆነው ጸሎታችሁ፣ በሃሳባችሁ እና በቻላችሁት ነገር ሁሉ ከጎናችን እንድትቆሙ በእናት ቤተ ክርስቲያን ስም ጥቄያችንን እናቀርባለን፡፡

በዚህ አጋጣሚ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በምናደርገው እና በምናቀርበው ጥያቄ ዙሪያ ከሕዝበ ክርስቲያኑ ጋር የምንመካከርባቸው ሰፋፊ መድረኮችን የምናዘጋጅ እንዲሁም ቢያንስ በአሥራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ የተለያዮ መንፈሳዊ እና ሕዝባዊ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የእያዳንዱን የውይይት ሂደት፣ውሳኔ፣ውጤት እና ቀጣይ አቅጣጫ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ምእመናን እና የኦርቶዶክሳዊያን ሰላም እና ድኅንነት የሚያስጨንቃቸው አካላት ሁሉ የውይይቱ አካል እንዲሆኑ ለማድረግ የምንጥር መሆናችንን ቃል እንገባለን፡፡

እግዚአብሔር አምላክ የቤተ ክርስቲያናችንን እና የአገራችንን ሰላም ይመልስልን!!!!

መስከረም ቀን በአዲስ አበባ የተጠራው የሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ

መስከረም 2 ቀን 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ